# ★ ዴሞክራሲያ ★

******************************************************

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ልሣን*

******************************************************

**ቅጽ 40 ልዩ ዕትም ቁ. 2** **ሐምሌ 2006**


## ሳይቃጠል በቅጠል!

አገራችን ኢትዮጵያ በጣም በአሳሳቢ ሁኔታ ላይ ትገኛለች። በሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ የፖለቲካ የበላይነቱን ጠብቆ ለመቆየት እንዲረዳው ሕዝብን በሕዝብ ላይ ለማነሳሳት ከፍተኛ ትንኮሳ እያደረገ ነው። ይህንን አሳሳቢ ሁኔታ፣ የዜጎች የእኩልነት መብት ተጠብቆና ተከብሮ እንዲኖር የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብም ሆነ የፖለቲካ ድርጅት ዝም ብሎ ሊመለከተው አይገባም።

በኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ዕምነት፣ ኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የተረጋገጠባት፣ ዴሞክራሲያዊት የሆነች፣ እኩልነትና ፍትኅ የሰፈነባት፣ በርግጥም ለሁሉም ዜጎች የጋራ የሆነች፣ ዕድገትና ብልጽግና ለሕዝቧ የሚዳረስባት፣ ሀገራዊ ነፃነቷ የተከበረና የግዛት አንድነቷም የተጠበቀ ሀገር ለማድረግ በቅድሚያ በዜጎቿ መካከል መስማማትና መቻቻል እንዲኖር ያስፈልጋል። የችግሮቻችን መፍትሂዎች ሁሉ ያሉት በመስማማታችንና በመቻቻላችን ላይ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለጥርጥር ብልኅነቱንና ታላቅነቱን በፈታኝ ወቅቶች ሁሉ ደጋግሞ ያረጋገጠ ስለሆነ ችግሮች ራሱ መፍታት እንደሚችል በእርግጠኝነትና በድፍረት መናገር እንችላለን። ሃሳብን በነፃነት የመግለጥ፣ የመሰብሰብ፣ የመደራጀት...ወዘተ ነፃነቱን ተቀዳጅቶ በአንድነት ለመምከር ከቻለ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበረሰባዊና ሌሎቹንም የፖለቲካ ችግሮች መፍታት ይችላል። ሀገሩን ከውጭ ወራሪ ለመከላከል ከባድ ዋጋን እንደከፈለ ሁሉ፣ ዛሬም ለሰላሙ፣ ለዴሞክራሲያዊና ለሰብዓዊ መብቱ፣ ለፍትሃዊነትና ለዜጎች እኩልነት ዋጋ መክፈል እንደሚኖርበትም ጠንቅቆ ያውቃል።

ባዕዳን በተለያየ ሽፋን (በትምህርት መልክ፣ በጥናታዊ ጽሑፍና በመጻሕፍት መልክ፣ አንዳንዴም አማካሪ ተብለው...ወዘተ) ያጎረሱንን፣ ካለማወቅም ሆነ ካለመብሰል ሳናላምጥ

በመዋጥ እንደ ሕዝብ የነበሩንንና ያሉንን የታላቅነታችንን መሠረቶች እንድንክድ፣ እንድናዳክም፣ አኩሪ ባህሎቻችንን እንድንጻረር ሆነናል።

ኢትዮጵያ ጥንታዊ ሀገር ነች፤ የጥንታዊነቷም ምንጭ ከትውልድ ትውልድ የዘለቀው የሁላችንም አባቶችና እናቶች ማንነትና ገድል ነው። ይህንንም የሚመሰክሩ በርካታ ከከርሰ-ምድሯ የሚወጡ ቅሪቶች/ግኝቶችና ሌሎች በገፀ-ምድሯ ላይ ያሉ ታሪካዊ ቅርሶችና ሥራዎች ያረጋግጣሉ። ቅድመ-አያቶቻችን በዓለማችን ቀደምት ከሚባሉት ሀገሮች አንዷ የሆነችውን ኢትዮጵያን እንደ አገር መሥርተው፣ ራሳቸውን እያስተዳደሩ ለመኖር የቻሉትና ሀገራቸውንም ከሌሎች ተቀናቃኞችና ወራሪዎች ጠብቀው ያቆዩዋት ብልኀና አርቆ አስተዋይ ስለነበሩ ነው። ኢትዮጵያ አኩሪ ታሪክና የበርካታ አሸብራቂ ባህሎች፣ ወግና ልማዶች፣ አያሌ የቋንቋዎች ዕድገትና ተወራራሽነት ተጣምረው የብዙ ደማቅ ኀብረ-ቀለማት ውበትን የተላበሰች ድንቅ ሀገር ነች። ከጥንታዊ ቅሪቶች እንደምንረዳው፣ የሃውልቶች፣ የግንቦችና ከንጥረ-ማዕድኖች የተሠራው ገንዘብ (የሚንት)…ወዘተ ባለቤት ናት።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ ከሚገኙት ሁለት ታላላቅ ተዛማጅ ቋንቋዎች ማለትም፣ ከ"ኒሎ-ሳህራዊና አፍሪካዊ-እስያዊ-ሴማዊ" ውስጥ የሚካተቱ ከ87 ያላነሱ ሕያው የሆኑ ቋንቋዎች ይነገሩባታል። እነዚህ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች፣ በመካከላቸው ካሉት ልዩነቶች ይልቅ ታሪካዊና መሠረታዊ ዝምድናዎቻቸው ወይም በዘር ግንዶቻቸው ተዛማጅነት ይበልጥ የተሳሰሩ ናቸው። ሁሉም ቋንቋዎች እስከነባህላዊ ገጽታዎቻቸው የእኛ ናቸውና እናከብራቸው፤ እናዳብራቸው። አርቆ ማየት የተሳናቸው ጠባብ ብሔረተኞች እንደሚሉት ልዩነቶቹ ግዙፍና አብሮ ለመኖር የማያስችሉ በፍጹም አይደሉም።

ከሕዝብ ቁጥርና የፍላጎቶች መጨመር ምክንያት የፍጆታም ሆነ የሌሎች ፍላጎቶች በተመጣጣኝ ደረጃ በቅርበት አለመገኘት ወይም ቶሎ አለማደግ የአንዱን ወይም የሌላውን ቋንቋ ተናጋሪ በፍላጎቱ ወይም በግፊት ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላው እንዲንቀሳቀስ በማድረጉ ከመስፋፋት ጋር መልክዓምድራዊ መራራቅም፣ ያለውን መጠነኛ የተፈጥሮ ሃብት መሻማት እየመጣ፣ አየልና ጠንከር ያለው በደል እያስከተለ መጋጨትን እየፈጠረ ቢመጣም፣ አብሮ መኖር ስላለ መሠረታዊ ዝምድናዎቻቸውን እንደያዙ ቋንቋዎችም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጡ፣ እያደጉና እየበዙም መጥተዋል። ይህ ታሪካዊ ክስተትና ሂደት ኢትዮጵያን በርካታ በፍቅርና በአንድነት ለዘመናት አብረው የኖሩ ጥንታዊና ሰፊ ብሄረሰቦችን ያቀፈች አንድ ሕዝብና ትልቅ ሀገር እንድትሆን አድርጓታል። ከቋንቋዎቻችን ቤተሰባዊ አንድነት፣ ከባህሎቻችን ተወራራሽነት ደግሞ የተለያዩ ባህላዊ

ዘፈኖች፣ ጣዕመ-ዜማዎችና አያሌ ውዝዋዜዎች መኖራቸው፣ ተነግሮለት የማያልቅ ውብ የባህል ክምችት ያላት ድንቅ አገር እንድትሆን አድርጓታል።

የፅሁፍን ጥቅም በመረዳት፣ ማንኛውንም ዕውቀትና መረጃ በሕዝቡ መካከልና ከትውልድ ወደ ትውልድ ጽፎ ለማስተላለፍ የሚያስችሉ ፊደሎች ለመቀመር የቻለ ሕዝብ ሀገርም ናት። ቅድመ-አያቶቻችን ፊደል ቀርፀው ብራናና ቀለምንም ሠርተው በዓለም ከሚታወቁ የጥንታዊ ጽሑፍ አንዱ ባለቤት እንድንሆን አድርገውናል። በዚህም ምክንያት የሥነ-ጽሁፍ ታሪካችንም ከሥነ-ቃል ታሪካችን ጎን ዋነኛውን የባህል ቦታ እንዲይዝ አድርጎታል።

የአያሌ ጥንታዊና ታላላቅ ሀገሮችን አመሠራረት ስንመለከት፣ ረጃጅም ጉዞዎችንና ፈርጀ-ብዙ ተግባራትን ያካተተ ነው። የኢትዮጵያን ሀገር መሆንና በሥርዓተ-መንግሥት ደረጃ መደራጀትም፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተከናወነ ተግባር ሳይሆን፣ ረጅም ጊዜን የወሰደና በርካታ ክንዋኔዎችን፣ ጦርነቶችንም ጭምር፣ ያካተተ ሂደት ነበር። ይህንን ተገንዝበን፣ ተምረንበት፣ የበለጠም ምርምር እያደረግንበት ከትውልድ ወደ ትውልድ ልናስተላልፈው የሚገባን ታሪካችን ነው። አንዱን ወይም ሌላውን የታሪካችን ገጽታ እየመዘዝን፣ ከብልህ ኢትዮጵያውያን በማይጠበቅ ደረጃ እርስ በርስ እየተጎዳዳን፣ በጎውን፣ ልንኮራበት የሚገባንን፣ ሀገራዊ ነፃነትን ተከላክሎ ማቆየትን ጭምር የሚገባውን ክብር ነፍገን፣ የጭቃ ጅራፍ ልናሳርፍበት አይገባም።

ኢትዮጵያ ውስጥ ብሄረሰቦች ኖረዋል፣ አሁንም አሉ፤ ወደፊትም ይኖራሉ። ሀገራችን የብዙ ብሄረሰቦች ሀገር መሆኗ እንደ አንዱ የሀገራችን ገጽታ ብሎም፣ እንደውበት ሊወሰድ ይገባዋል እንጂ የችግር ምንጭ ሊሆን አይገባውም። ከዚህም በላይ፣ የትኛውም ኢትዮጵያዊ ንፁህ አፋር፣ ንፁህ አማራ፣ ንፁህ ሲዳማ፣ ንፁህ ኦሮሞ፣ ንፁህ ትግሬ፣ ንፁህ አገው…ወዘተ አይደለም። ብሄረስቦች በጋብቻ፣ በሃይማኖት፣ በሙያ፣ በአኗኗርና በመሳሰሉት ለዘመናት በዳበረ ትስስር አሁን ያለውን የሀገራችንን ኅብረተስብ በጋራ መገንባት ችለዋል። ይህ ትስስር በተለይም ከከተሞች ማደግ ጋር ተያይዞ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ አርሶአደሮች፣ ሠራተኞች፣ መለዮ-ለባሾች በሙያቸው ሴቶችም በፆታቸው…ወዘተ በመሰል ማኅበሮች ሲደራጁ፣ እያንዳንዳችን ኢትዮጵያውያን በበርካታ ማንነታችንን ሊገልጡ በሚችሉ ማኅበረሰባዊ ትስስሮችን ፈጥረናል። ታዲያ በምን ተአምር ነው፣ ከበርካታ የማንነታችን መገለጫዎች አንዱን፣ የብሄረሰብ ማንነታችንን ብቻ ነጥለን በማውጣት፣ ሀገራችንን ማፍረሻና እርስ በርስ ለመጋጨት የምንጠቀምበት?

በሃይማኖት ረገድም፣ በዓለማችን ካሉት ዋና ዋና ሃይማኖቶች ኢትዮጵያውያን ሦስቱን ማለትም አይሁዳዊነትን፣ ክርስትስትናንና እስልምናን በተለያዩ ወቅቶች በመቀበል ኖረዋል። ጥንታዊ ዕምነቶችን የሚከተሉ፣ በቁጥር አነስ ያሉ ኢትዮጵያውያንም ወጣ ወጣ ባሉት የሀገራችን ዳርቻዎችና አልፎ አልፎም በየመሀሉም አካባቢዎች፣ በምንም መለኮታዊ ኃይል የማያምኑ፣ አይብዙ እንጂ አሉ። በእርግጥ በተለያዩ ዕምነት ተከታዮች መካከል ፉክክርና ግጭቶች ተነስተው እንደነብር በታሪክ ተዘግቧል። ከእነዚህም ግጭቶች ውስጥ ጥቂቶቹ ከበድ ያሉ እንደነበሩ፣ መንግሥትና ሃይማኖት በመቆራኘታቸው ምክንያት የሃይማኖት እኩልነት እንዳልነበረ ቢታወቅም፣ አገራችን በአካባቢ ካሉ ሀገሮች ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ የተለያዩ ዕምነት ተከታዮች ተቻችለው የኖሩባትና ዛሬም የሚኖሩባት ሀገር ነች። እውነቱ ይህ ሆኖ እያለ፣ ዛሬ የጥፋት መልዕክተኞች የቋንቋን፣ የብሄረሰብንና የሃይማኖት ልዩነቶችን በመጠቀም ሕዝብን ከሕዝብ ማናቋርያ መሣሪያ እያደረጉ እንደሆኑ እየታየ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) በብሄረሰቦችና በሃይማኖት እኩልነት ያምናል። ከቀድሞ ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ምንም ዓይነት የብሄረሰብና የሃይማኖት ጭቆና እንዳይኖር ታግሏል፤ በትግሉም ውስጥ ከባድ መስዋዕትነት ከፍሏል። አሁንም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በብሄረሰብ ምንጩ ወይም ማንነቱ፣ በቋንቋው፣ በሃይማኖቱ ወይንም በዕምነቱ፣ በፆታው፣ ወይም በመደቡ መሠረት መጨቆን የለበትም ብሎ ያምናል። ሁሉንም ዓይነት ጭቆና በመቃወም ለሕዝቡ እኩልነት አምርሮ ይታገላል። ጠባብ ብሄረተኛነት ኋላቀርና ጎጂም የፖለቲካ አስተሳሰብ ነው። ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ጠባብ ብሄረተኝነትንም አምርሮ በመቃወም ከፍተኛ መስዋእት ከፍሏል። ሆኖም ግን የጠባብ ብሄርተኝነትን ጎጂነት በትግል ታሪኩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በበቂ ባለማሳየቱ ስህተት እንደነበር ዛሬ ካላይ ቆሞ ያለፈውን ታሪኩን ሲገመግም ይመለከታል።

በየትኛውም የዓለም ክፍል፣ ጠባብ ብሄረተኛነት እንደ አንድ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ከተስፋፋ፣ ውጤቱ እርስ በርስ መበጣበጥ፣ ሲብስም መተላለቅ ነው የሚሆነው። ስለዚህም ይህንን የህወሓት መሪዎችና በእነሱ የሚታዘዙ ጠባብ ቡድኖች በኢትዮጵያ ውስጥ የረጩት መርዝ ጎጂነቱ ለሁሉም መሆኑን ተረድተን በጋራ እናምክነው እንላለን።

በኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) እምነት ኢትዮጵያዊ ሁሉ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል ሠርቶ፣ ሀብትና ንብረት አፍርቶ የመኖር መብቱ የተጠበቀ መሆን አለበት። የህወሓት አገዛዝ አንተ

ከዚህ ጎሣ ነህ፣ አንተ ደግሞ ከዚያኛው ነህ ስለዚህ ወደ ክልልህ ሂድ እየተባለ ለረዥም ዓመታት ከኖረበት ቀየው ንብረቱን እየተቀማ እንዲባረር የሚደረገው ዘርን መሠረት ያደረገው አገዛዝ ነው። ይህንን አገዛዝ ሕጋዊ ለማድረግ የተነደፈውና ሀገሪቱን በዘር ፖለቲካ ከፋፍሎ አደጋ ላይ እየጣላት ያለው ሕገ-መንግሥት መለውጥ አለበት።

የህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች እስከዛሬ በታየው ተጨባጭ ሥራቸው በትውልድ ኢትዮጵያውያን ቢሆኑም፣ የኢትዮጵያዊነት ዕምነትና ሀገራዊ ስሜት ግን የሌላቸው ናቸው። እርስ በርስ ሊያባሉንና ሀገራችንንም ለጥፋት ሊዳርጓት ተግተው እየሠሩ ይገኛሉ። በትግራይ ውስጥ በመለስና ዓባይ ፀሓዬ ይመራ በነበረው የቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ቡድን ተዘጋጅቶ ይዘመርለት የነበረው "በሏቸው፣ በሏቸው እነዚህን አማሮች!" የሚል ነበር። በዚህም በጠቅላላ አማርኛ ተናጋሪ የሆነው ሕዝብ ነው እንደ ጠላት እንዲታይ ለማድረግ የሞከሩት። አማርኛ ተናጋሪዎችና ትግርኛ ተናጋሪዎች በጭራሽም ጠላት ሆነው አያውቁም፤ አንዱ ብሄረሰብ የሌላው ጠላት አይደለም፤ በሺህ ክሮች የተሳሰሩ ወንድማማቾችና እህትማማቾች ናቸውና። የአገዛዙ ዓላማ ኢትዮጵያዊነትን ከሕዝቡ አዕምሮ በማደብዘዝ ሀገሪቱን ለማፈራረስ ነው። የምሥራቁን ሀገራችን ክፍል ገንጥለው ከሶማሌ ጋር ለማዋሃድ ይሠሩ የነበሩትን የሲያድ ባሬን ተዋጊዎችና አዝማቾች በፊት ያነገቡትን ዓላማቸውን ሳይተዉ፣ መልሰው በሐረርጌ ውስጥ የሥልጣን ባለቤቶች እንዲሆኑ አድርገዋቸዋል።

ህወሓት የተባለውን ጠባብ ብሔረተኛ ድርጅት፣ ከመሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ፣ መሰሪ መሪዎች፣ እንኳንስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ በስሙ ለሚነግዱበት ለትግራይ ሕዝብ እንኳን ከልባቸው ቆመውለት አያውቁም። ለትግራይ ሕዝብ ፍቅር ቢኖራቸው ኖሮ በውሸት ከውጭ ዕርዳታ መጥቶልሃል ብለው ሕዝቡ በብዛት ወደ ሱዳን ወዲ-ከውሊ...ወዘተ ወደሚባሉ ሥፍራዎች ወጥቶ በረሃብ እንዲያልቅ አያደርጉም ነበር። ከዚያም በተጨማሪ፣ የትግራይ ወጣት ኤርትራ ሂዶ ሻዕቢያን በማገዝ በጦርነት እንዲማገድ አያደርጉም ነበር። ህወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ወቅት ጀምሮ ሆን ብሎ የዘር ጥላቻን ሲቆሰቁስ ቆይቶ በርካታ ጭፍጨፋዎችን አካሂዷል። በተለይ ሁለቱን የኢትዮጵያ ትልልቅ ብሄረሰቦች፣ ኦሮሞንና አማራን፣ ለማፋጀት እስከዛሬ ድረስ ያለመታከት እየሠራ ነው። ሁለቱ ብሄረሰቦች ተጠፋፍተው፣ ቀሪው ሕዝብና ሀገሪቱ ከጉዳትና ከመጥፋት ይድናሉ ማለት ዘበት ነው። የኢትዮጵያ ጠላቶች (ጣሊያኖች፣ ግብፃዊያኑ...ወዘተ) ኢትዮጵያውያኑን ለመከፋፈልና ለማጋጨት የጣሩት ከፋፍለውን አዳክመውን ለመግዛትና ለመበዝበዝ ነበር፤ የዛሬዎቹ አገር-በቀል ገዥዎችም የባዕዳኑን ፈለግ የተከተሉት ለመከፋፈልና ለማጋጨት ነው። የህወሓት መሰሪና ጨካኝ መሪዎች ዓላማ ሕዝቡን እርስ በርስ አባልተው ሀገራችንን ማጥፋት ነው።

ለማንም የማይሳሱ፣ የሰብዓዊነት ጥንፋሬ የሌላቸው ስለመሆናቸው ደግሞ ከተግባሮቻቸው የበለጠ ማስረጃ የሚያስፈልግ አይመስለንም።

“መሬት አትንጠቁ!” ብለው የተቃውሞ ሰልፍ ባደረጉ ወጣቶች መካከል ሰርገው በመግባት የአድዋን ድል መሪ የምኒሊክን ሃውልት "ይፍረስ" የሚል መፈክር በማስያዝ ወያኔና ተለጣፊዎቻቸው የጥያቄው አቅጣጫ እንዲቀየርና ሕዝብ ከሕዝብ እንዲጋጭ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። የአድዋ ጀግኖች የመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ ጀግኖች በመሆናቸው ወጣቶቹን ትክክለኛውን ታሪካቸውን እንዲያውቁ እንደማድረግና ለጥያቄዎቻቸው ተገቢ መልስ እንደመስጠት ፋንታ ወደ ጥላቻ መንፈስ ሊያስገቧቸው እየጣሩ ይገኛሉ። ዛሬ የኦሮሞ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ጥያቄ በምንም ተዓምር የሃውልቶች መፍረስ ወይም መገንባት ጥያቄ ሊሆን አይችልም። የወጣቱ ጥያቄ የሥራ አጥነት ጥያቄ ነው፤ የዴሞክራሲ፣ የሰብዓዊ መብት፣ የህግ የበላይነትና በገዛ ሀገሩ እንደዜጋ ተከብሮ የመኖር......ወዘተ ጥያቄ ነው። ይሁን እንጂ የህወሓትና መሰል ድርጅቶች መሪዎች ያልተረጋገጠ ታሪካዊ ክስተቶችን ፈልገው አኖሌ ላይ ሀውልት ለመገንባት ያነሳሳቸው የሕዝቡ መሠረታዊ ፍላጎትና የችግሮቹ መፍትሄ ሆኖ ሳይሆን ቋሚ የጥላቻ መርዝ መትከል ስለፈለጉ ነው።

ከአገራችን የታሪክ አሻራ እንደምንረዳው አንድ ኃይለኛ ከደቡብ ኢትዮጵያ ሲነሳ እስከ ሰሜን ጫፍ ዘልቆ ሲያስገብር፣ አልገብር ያለውንም እያሠረና እየገደለ መግዛቱን፤ ከሰሜንም ሲነሳ እንደዚሁ እስከ ደቡብ ድረስ ዘልቆ ማስገበሩን ነው። ከምሥራቅም የተነሳ ኃይልም መላውን አገራችንን አስገብሯል። በዚያ የማስገበር ጉዞ ውስጥ ሕይወትና ንብረት ለመጥፋቱ አጠያያቂ አይደለም። ይህ ደግሞ በኢትዮጵያ ብቻ የተደረገ ሳይሆን በማንኛውም አገር ታሪክ ውስጥ የታየ ሃቅ ነው። ዛሬ በዓለም ላይ በሳይንስና ቴክኖሎጂ አድገው የምናያቸው አገሮች፣ በእንደዚህ ያለ የታሪክ ሂደት ውስጥ አልፈው ነው ከዚህ የደረሱት። ታሪክን ለታሪክ ፀሐፊዎች ትተን፣ ዛሬ በ21ኛው ክፍለ ዘመን አጉልተን ልናስተምርና ልናሳድግ የሚገባን፣ መጠፋፋቱን ሳይሆን ያስተሳሰረንን የአንድነት እትብታችንን ታሪክ መሆን አለበት።

በጠባብ ብሄረተኛነትና አድላዊ ዕምነታቸው የህወሓት መሪዎች የአዲስ አበባ ኗሪዎችን መሬት ከባለንብረቶቹ ቀምተው “አልሚዎች” ለሚሏቸው ተከታዮቻቸው እያከፋፈሉ ነው። ዛሬ የአዲስ አበባ መሬት ሲያንሳቸው የአካባቢ ገበሬዎችን የእርሻ መሬት ነጥቀው ያንኑ ተግባራቸውን በዕብሪት መቀጠል ፈለጉ። የዘር ጥላቻን እንደወተት እየጋቱ ያሳደጓቸው ወጣቶች፣ በየከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች ውስጥ ለመከፋፈያ ዓላማቸው እንዲያመች በየብሄረሰብ ከፋፍለው ነውና ያደራጇቸው፣ የእነሱንም ጥፋት ታዝበው አላለፏቸውም። ዛሬ

ያልጠበቁት ተቃውሞ በእነሱም ላይ ሲመጣ፣ ተደናግጠው የወጣቶቹን በገዥዎች ላይ ያነጣጠረ ቁጣ ወደ አማራው ለማዞር በመሞከር ላይ ናቸው። የህወሓት መሪዎችና ታዛገሮቻቸው፣ ምንም ዓይነት ሰብዓዊነት ስለሌላቸው፣ ወጣት ተማሪዎቹን የጥይት ናዳ አወረዱባቸው! እነዚህ ወጣት ኢትዮጵያውያን ለምን ይጨፈጨፋሉ? ከኢትዮጵያውያን አብራክ የወጡ ወጣቶች ወገኖቻችን ናቸውና አትንኳቸው፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል የጥላቻ መርዝ ማርከፍከፉም ይብቃችሁ እንላቸዋለን።

ጠባብ ብሄርተኝነት በርግጥም መርዘኛ ነው፤ ስለዚህም ጎጂ ነው። እርስ በርስ መጋጨቱ ለማንም አይበጅምና ስህተት ላይ አንውደቅ። ጠባብ ብሄረተኞችን አምርረን እንታገላቸው! ተማሪዎችን፣ መምህራንን፣ ሥራ አጦችን፣ አርሶአደሮችንና ምዕመናኑን በየተራ እያሳደዱና እየገደሉ በሰላም መኖር እንደማይችሉ ልናሳያቸው ይገባል። ህወሓት በሕዝባችን ላይ እየፈጸመ ያለው በደል ከተካው የደርግ አገዛዝ ይበልጥ እንደሆነ እንጂ አያንስም። ደርግ የሚበልጣቸው እየጨፈጨፈ “የፍየል ወጠጤ ” በሚል ዜማ በራዲዮ በማጀቡ ብቻ ነበር።

ኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ዕድገት ያላገኘችው ለምንድነው? እስከመቼ ነው አብዛኛው ዜጋ በችግር፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩት ደግሞ በረሃብ እየተቆሉ የሚኖሩት? እንዴት ሕዝባችንን ለመመገብ አልቻልንም? አገራችን ከጥንታዊነቷና ታሪካዊነቷ ጋር የሚመጣጠን የዕድገትና የልማት ደረጃ ለምን ለመድረስ አልቻለችም? ስለዚህም ዛሬ መጠየቅና መቸገርም ያለብን ሁላችንም እየፈለግነው ሳናገኘው የቀረነውን፣ የሚያስፈልገንን፣ የሚጠቅመንና፣ የሚያሻሽለንን፣ የሁለንተናዊ ዕውቀት፣ የሁለ-ገብ ልማትና ዕድገትና ዘላቂ የሰላም፣ ዒላማዎችንና ግቦችን ነው። የዜጎች በነፃነት መኖር፣ ሙሉ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብትን መቀዳጀት፣ አብዛኛው ሕዝብ የሚመርጠውንና የሚፈልገውን የፖለቲካና ማኅበራዊ ሥርዓት ለመገንባት ያስችለናል። ይህንን ሕዝብ የሚመርጠውን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን እንዳይሆን ካደረጉት ውስጠ የዜጎች ነፃነት ማጣት፣ በአምባገነናዊ ገዥዎች ዴሞክራሲ መነፈግ፣ ጠባብ ብሄረተኛነት እንደ መሪ የፖለቲካ አስተሳሰብ በሕዝብ ላይ መጫኑ፣ የሕግ የበላይነት አለመኖር፣ ለሀገር ተቆርቋሪነትና የኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብና ስሜት በሌላቸው ስመ-ኢትዮጵያውያን መገዛት፣ የመልካም አስተዳደር ዕጦትና የገዥዎች አድላዊነት፣ ሙስና፣ የሀገራዊ ሉዓላዊነት ስሜት መክኖ የባዕዳን መጠቀሚያ መሆናችን፣ ማለቂያ የሌለው የወጣቱና የተማረው የሰው ኃይል ፍልሰትና የመሳሰሉት ናቸው። ትልቁና ዋነኛው ከድህነትና ከኋላቀርነታችን እንዳንወጣ ያደረገን ምክንያታዊ ችግር ሕዝቡ የሥልጣን ባለቤትነቱን ስላልተቀዳጀ ነው።

ገዥዎች፣ ቀድሞም ሆነ አሁን፣ በሕዝቡ ጫንቃ ላይ ተጭነው እንዳሻቸው ሲገዙት፣ ሲበድሉትና ሲመዘብሩትና ስለኖሩ፣ በሕዝቡ ስም የሉዓላዊነትን ሥልጣን ይዘው እንዳሻቸው ተገልግለውበታል። የአሁኖቹም እንደ ቀድሞው እየተገለገሉበት ይገኛሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም እንኳን ሀገራዊ ነፃነቱን አስከብሮ ቢኖርም፣ የሥልጣን ባለቤትነትና ሉዓላዊነቱን ግን ገና ስላልተቀዳጀ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቱን ለመቀዳጀት ከፍተኛ ትግል ማድረግ ይኖርበታል። የሕዝቡ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነት ሲረጋገጥ፣ የሚተዳደርበትን መንገድና አቅጣጫ (ፖሊሲ) ነፃ ሆኖ በተወካዮቹ አማካይነት ሊወስን ሲችል፤ ተወካዮቹንም በነፃ፣ ርቱዓዊና ተዓማኒነት ባለው ምርጫ አማካይነት ለመምረጥ ሲችል ብቻ ነው ሀገራችን መበልጸግ፣ የሕዝቡም ሕይወት መሻሻል የሚችለው እንጂ ጥቂት የገዥው መደብ አባላት በዘረፉ ስለከበሩ ሀገር አደገች ማለት አይቻልም። የሕዝቡ የሥልጣን ባለቤት መሆን ለሀገራችን አንድነት እጅግ በጣም አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ ወሳኝም ነው። ሀገራችን ከባዕዳን የእጅ አዙር ቁጥጥር፣ ሕዝባችንም ከገዥዎች ጭቆና ነፃ ሊሆኑ የሚችሉት ሕዝቡ የሥልጣን ባለቤት ሲሆን ብቻ ነው።

ሀገራችን ያላትን የተፈጥሮ ሀብት (መሬት፣ ውኃ፣ ደን፣ የከርሰ-ምድር ማዕድናት፣ ለምሳሌ ወርቅ፣ አልማዝ…ወዘተ) ለሀገር ልማት በማዋል ለመጠቀምም ሆነ፣ የተደበቁትን ከከርሰ-ምድር ፈልጎ ለማግኘት እስካሁን አለመቻሉ ከሥርዓቱ አምባገነናዊነት ጋር ይያዛል። በህወሓት ውስጥ የፀረ-አንድነቱ ክንፍ፣ ማለትም የተገንጣይነት ዓላማን ያነገበው፣ ቡድን አይሎ መውጣት፣ በፊት በኤርትራው ነፃ አውጭ ድርጅትና በደጋፊዎቹ በዐረቦች፣ በኋላም በምዕራባውያኑም ጭምር ታግዞ ለሥልጣን መብቃት፣ ቡድኑም በአጋፋሪነት ተሰልፎ ኤርትራን ማስገንጠሉ፣ የሀገሪቱን አንድነት ለማናጋት ሆን ብሎ የሚሠራ ኃይል የማይወዳትን ኢትዮጵያን የሚገዛበት ሁኔታ መፈጠሩ፣ ለኢትዮጵያ የዛሬ ችግሮች መነሻና ትልቅ ያልተፈታ ተቃርኖ ነው።

ሀገራችንን የተለያዩ የውጭ ወራሪዎች ህልውናዋንና አንድነቷን በተፈታተኑባቸው አያሌ ወቅቶች (የቱርክና የግብፅ) የቀይ ባሕር በራችንን የመያዝ ጥረቶች፣ በአድዋው ድል የከሸፈው የጣሊያን ወረራ፣ የፋሽስት ጣሊያን ድጋሚ ወረራና እንግሊዞች የሞግዚትነት አስተዳደር ለመጫን ያደረጉት ሙከራ፣ እንግሊዞች ከፊል ሐረርጌን "ሃውድ" የሚል ልዩ መጠሪያ ሰጥተው የኰተኰቱት የሌላነት ስሜት ሰንኰፉ እስከዛሬ አለመነቀሉ፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ የሶማሌው ሲያድ ባሬ በባዕዳን ታግዞ ያደረገው ወረራና አሁን በአካባቢው ያለው የተገንጣዮች እንቅስቃሴ ባዕዳን ተስፋፊዎችና ቅኝ ገዥዎች የሃይማኖት ማስፋፋትን በተለያዩ ወቅቶች እንደመሣሪያ ለመጠቀም በሞከሩበት ጊዜ ሁሉ ሕዝቡ በአንድነት በመቆም ድባቅ መትቶ

አሳፍሯቸዋል። በተለያዩ ጊዜያት ቱርኮች፣ ግብፆች፣ ፖርቱጋሎች፣ ጣሊያኖች፣ የሱዳን ማህዲስቶች፣ የጀርመን ሉተራኖች…ወዘተ በሃይማኖት ማስፋፋት ከለላ የሚደረጉ የመተናኮስ፣ ሕዝቡን የመከፋፈልና እርስ በርስም የማቃረን ሙከራዎችን ሁሉ አድርገዋል። እንደዚህ ያሉ ተንኮሎችና ሤራዎች ወደፊት አይሞከሩም ማለት አይቻልም። በቅርቡ የግብፅ ፖለቲከኞች በዓባይ ጉዳይ ላይ ሲነጋገሩ ሾልኮ ከወጣው ሃሳባቸው አንዱ ሃይማኖትንም መጠቀም፣ (የብሄረሰብ ልዩነትን ከማባባስ በተጨማሪ) እንደሚያልሙ ተስተውሏል።

ኤርትራን፣ ለማስገንጠል የተደረገ ከፍተኛ ሤራ፣ ኢትዮጵያን ስትራቴጂያዊ ጉዳት ላይ ጥሏታል። ከህወሓት በፊት የነበሩት ሁለት መንግሥታት የኤርትራን ችግር ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ከመፍታት ይልቅ በጦርነት ለመፍታት ያደረጉት ጥረት እራሱን የቻለ አሉታዊ ተጽዕኖ ቢኖረውም፣ እንደ ህወሓት ሀገሪቱን ለዘላቂ ስትራቴጂያዊ ጉዳት ላይ ግን አልጣሏትም።

የኤርትራ መገንጠል በዓለማችን ታይቶ በማይታውቅ ደረጃ “እባካችሁ እወቁልኝ” ብሎ የተባበሩት መንግሥታትን የጠየቀው ይኸው አሁን በሥልጣን ላይ ያለው ከሃዲ ቡድን ነው። በአዲስ ድንበር ክልል የተቆረጡት ሳሆዎች፣ ትግራይ-ትግሪኞች (ትግሬዎች)፣ አፋሮች፣ ኩናማዎች፣ የኤርትራ አገዎች (ቢሌኖች)…ወዘተ መነጠሉን በእርግጥ ይሹታል ማለት ይቻላል? ይህ በኤርትራ መገንጠል የተፈጠረው ውስብስብ ችግር ወደፊት ለአንዴና ለሁልጊዜ መፈታት ያለበት ነው። ከዘጠና አራት ሚሊዮን በላይ የሆነ ሕዝብ፣ ከስትራቴጂያዊ ጥቅም አኳያ በጣም ጎጅ ከሆነ ሁኔታ ቀልጠፍ ብሎ ነገር ግን በጣም በሳል በሆነ ስልት ሊወጣ የሚችልበት ሁኔታና መንገድ መገኘት አለበት። ዛሬ ትልቅ ግንዛቤ ሊያገኝ የሚገባው ችግር ኢትዮጵያ በሀገር-በቀል ጠላቶቿ እጅ የመውደቋ ክስተት ነው። ማንኛውም ግለሰብ በህወሓት/ኢህአዴግ ለመታመንና ለመሾም ዋናው መመዘኛው ኢትዮጵያን መጥላት በመሆኑ፣ ይህ ሕያው ተቃርኖም በቅድሚያ ሊፈታ ይገባል።

ጠባብ የብሄረሰብ አስተሳሰብን ኮትኩቶ በማሳደግ፣ በሕዝቡ መካከል ያለውን ትስስርና የአብሮ-መኖር ፍላጎትና ስሜትን በመቦርቦር፣ የሚያቃቅሩትንና የሚያጋጩትን ሆን ብሎ በማጉላት፣ ወደ ተገንጣይነት ዓላማ የማሳደግ፣ አንዱ ብሄረሰብ ሌላውን እንዲጠላና ብሄረሰቦች እርስ በርስ እንዲጋጩ ለማድረግ ቀን ከሌት ተግቶ የሚሠራ ገዥ ቡድን ነው ዛሬ ሀገራችንን እየገዛም፣ እያጠፋም ያለው። ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚሠራ ኃይል ደግሞ ኢትዮጵያን አግባብ ባለው መንገድ ሊያኖር፣ ሊያስተዳድርና ሊያሳድግ አይችልም። ስለዚህም የአገዛዙ ከሥልጣን መወገድ ለሀገሪቱ ኅልውናም ጭምር አስፈላጊ ነው።

ከኢትዮጵያ ወደ ተለያዩ የጎረቤት ሀገሮች የሚፈሱት ወንዞቿ፣ በተለይም ከምዕራብ የሚፈሰውን ዓባይና በተወሰነ ደረጃም ወደ ደቡብ (ሩዶልፍ ሃይቅ) የሚፈሰው የኦሞን ወንዝ ውኃ አጠቃቀምን በተመለከተ ገና ፍትሃዊና ሚዛናዊ ድርድሮች ባለመደረጋቸው፣ ሁልጊዜም ግጭቶችን ጋባዥ የሆኑ የፖለቲካ ውዝግቦችን ሊያስነሳ መቻሉና፣ በተለይም ግብፅና ሱዳን ኢትዮጵያን ለማናጋትና ለማዳከምም የእጅ-አዙር ሤራዎች እንዲያውጠነጥኑ በተደጋጋሚ መጋበዙ፣ ኢትዮጵያን እጅግ በሚጎዳ መልኩ ከሱዳን ጋር በሚስጢር፣ ከሕዝቡ በስተጀርባም የድንበር መስመሮችን ለመካለል ስምምነት ላይ ደርሶ፣ ቀደም ብሎ የገባውን የሀገር ክህደት ደባ ህወሓት/ኢሕአዴግ ዛሬም በተግባር እየፈጸመው ነው። በአመዛኙም ውኃ-ገብና ደን-ለበስ የሆነ ሰፊ ለም መሬታችንን አሳልፎ የሚሰጥ ስምምነት አድርጓል። ይህንን ሊያውገረግር ቢሞክርም፣ ሊሸፋፍነው የማይቻለው ትልቅ የሀገር ክህደት ወንጀል ነው። የህወሓት መሪዎች የሕዝብ ውክልና ሳይኖራቸው ይህን በማድረጋቸው የኢትዮዮጵያን ሀገራዊ ሉዓላዊነትና አንድነት ደፍረዋል፤ የሕዝቡንም ሥልጣንና መብት ጥሰዋል።

ሀገራችን የብዙ ብሄረሰባት ሀገር እንደመሆኗ መጠን አንድ ጠባብ ብሄርተኛ ቡድን የሀገሪቱን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚዊና ማህበራዊ ክፍሎች በብቸኛነት በመሣሪያ ኃይል በመያዝ ከዘጠና አራት ሚልዮን በላይ የሆነ ሕዝብን እጣፈንታ ተቆጣጥሮ ብዙም መቆየት አይችልም። ይህንንም አሁን በሥልጣን ካለው አገዛዝ በፊት የነበሩት የአፄውና የወታደራዊው መንግሥታት አስከፊ አወዳደቅ በተግባር አሳይተውታል። በሌላ በኩል ደግሞ በዘመናት በተለያዩ ሁኔታዎች በተጋመዱ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ነጣጥሎና ለያይቶ ለየብቻቸው እንዲቆሙ ማድረግም በፍጹም የሚቻል አይሆንም። ይልቁንስ፣ ዛሬ ሀገራችን ከምትገኝበት አሳዛኝ ሁኔታ እንድትላቀቅ፣

1ኛ) የዜጎችን እኩልነት እውን ማድረግ፣

2ኛ) አሳታፊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መመሥረት፣

3ኛ) የሕግ የበላይነትን፣ የሰብዓዊ መብትን ..... ወዘተ እውን ማድረግ፣

4ኛ) መንግሥትና የሃይማኖትን መለያየት፣ የዕምነት ነጻነት እንዲኖር ማድረግ፣

5ኛ) ጠባብ ብሄርተኛነት የሚነጣጥልና ሁላችንንም ሆነ እያንዳንዳችንን የሚያዳክም መሆኑን ተረድትን በጋራ ብሄራዊ ራዕይ ላይ ማተኮር፣

6ኛ) ለዘመናት ያፈራናቸውን የጋራ እሴቶቻችንን ጠብቀንና ተንከባክበን ሀገራችንን መገንባት ይኖርብናል።

**ይህንንም ለማድረግ ቁልፍና ብቸኛው አማራጭ ደግሞ በቅድሚያ የህወሓት/ኢህአዴግን አገዛዝ በመቃወም ላይ ያሉትን ኃይሎች ሁሉ በአንድነት ግልፅ ባሉ የጋራ ሀገራዊ ዓላማዎች ላይ ባተኮረ ሰፊና ጠንካራ ኃይል ሥር ለማሰባሰብ ከፍተኛ ጥረትና ርብርቦሽ ማድረግ ነው። ከዚያም ሕዝቡ የጋራና ሀገራዊ ዓላማዎቹን የራሱ አድርጎ ከያዛቸው ቀሪው ሥራ የሚከብድ አይሆንም።**

**የተባበረ የሕዝብ ትግል ምንጊዜም አቸናፊ ነው!**